# ለዳሸን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳሸን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 27ኛ (ሃያ ሰባተኛ አስቸኳይ) ጠቅላላ ጉባዔ ሐምሌ 17 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊኒየም አዳራሽ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓት እና ቦታ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል።

| | |
|---|---|
| የአክሲዮን ማኅበሩ ስም | ዳሸን ባንክ አ.ማ. |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ዓይነት | የባንክ ሥራ ውስጥ የተሰማራ የአክሲዮን ማኅበር |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 14,336,972,000.00 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር | 04/2/01821/88 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ድረ-ገፅ | www.dashenbanksc.com |
| የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ | አዲስ አበባ ፣ ልደታ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 09፣ የቤት ቁጥር አዲስ |

## የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም

2. ምዕላተ ጉባዔውን ማረጋገጥ

3. የጉባዔውን አጀንዳ ማፅደቅ

4. የዳሸን ባንክ አ.ማ. የመመስረቻ ፅሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብን ስለማሻሻል፤

5. በ22ኛው አስቸኳይ የባንኩ ባለአክሲዮኖች የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የተደረገውን የካፒታል ጭማሪ ተከትሎ በውርስ እና በሽያጭ የተላለፉ አክሲዮኖችን በተመለከተ ተወያይቶ ማፅደቅ፤

6. ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በ26ኛው አስቸኳይ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የባንኩን ካፒታል ማሳደግን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ በከፊል ሰለማሻሻል፤

7. የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ማፅደቅ

## ማሳሰቢያ

• በጉባዔው ላይ በግንባር መገኘት የማይችሉ ከሆነ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፊት ለፊት በሚገኘው የዳሸን ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት 14ኛ ፎቅ የቦርድ ፅ/ቤት በመቅረብ የውክልና ቅፅ በመሙላት ከስብሰባው ከሶስት ቀን በፊት ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።

• በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባዔው በአካል የምትገኙ ባለአክሲዮኖች ማንነታችሁን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ ሕጋዊ ውክልና ይዛችሁ ለምትቀርቡ ተወካዮች የወካያችሁን ማንነት የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን።

• በውል አዋዋይ የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ ዋና ማስረጃውን እና ኮፒውን ይዞ በመቅረብ በስብሰባው ላይ መሳተፍ ይችላል።

• በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ሕግ መሠረት አክሲዮኖችን በኤሌክትሮኒክስ የምዝገባ ሥርዓት ለመመዝገብ የፋይዳ (ብሔራዊ መታወቂያ) ስለሚያስፈልግ በዕለቱ ሁሉም ባለአክሲዮኖች የፋይዳ መታወቂያችሁን ይዛችሁ በስብሰባው እንድትገኙ እናሳስባለን።

• በተራ ቁጥር (4) ላይ የተጠቀሰውን የመመስረቻ ፅሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያን በተመለከተ የተዘጋጀውን ሠነድ ከባንኩ ድረ-ገፅ (www.dashenbanksc.com) ላይ ወይም በዳሸን ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት 14ኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው የቦርድ ፅሕፈት ቤት በአካል በመቅረብ ማግኘት ይቻላል።

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**
**ዳሸን ባንክ አ.ማ.**